M O N T G O M E R Y C O U N T Y P U B L I C S C H O O L S

# **East Silver Spring Elementary School**

631 Silver Spring Avenue, Silver Spring, MD 20910 240-740-0620 Fax: 301-650-6424

December 4, 2019

ውድ ወላጆች እና አሳዳጊዎች፡-

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) የ 2019 አካውንቴቢሊቲ ሪፖርት ካርድ በሜሪላንድ ስቴት ለሚገኙ ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት አስተላልፏል። የ 2019 የሜሪላንድ ሪፖርት ካርድ ለ **East Silver Spring Elementary School** በዚህ አገናኝ መስመር ሊገኝ ይችላል፡-

የሜሪላንድ ሪፖርት ካርድ ዲዛይን የተደረገው የትምህርት ቤቶችን ስኬታማነት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ እና የሒሳብ የስቴት ቴስት/ፈተና ውጤቶችን መመዘን፣ ድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁነት፣ እንግሊዝኛ የሚማሩት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት የስኬት ደረጃ፣ የሚመረቁ ተማሪዎች ብዛት፣ እና ለሁለገብ ትምህርት ተማሪዎች ያላቸው ተደራሽነት እና የሚያገኙት ክሬዲት በብዙ መንገዶች ለመገምገም ነው።

ተጨማሪ ብቃት/ቅልጥፍና አመላካቾች በ 2019 የሜሪላንድ ሪፖርት ካርድ ላይ የተጨመረ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ለኤለመንተሪ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የአካዳሚክ እርምጃ አመላካች በአሁን ጊዜ የ5ኛ እና 8ኛ ክፍሎች በስቴት የሳይንስ ፈተናዎች/ቴስቶች የተማሪ ብቃት ደረጃን ያካትታል። የትምህርት ቤት ጥራት እና የተማሪ ስኬታማነት አመላካች አሁን የሜሪላንድ ትምህርት ቤት ዳሰሳን፣ የተማሪዎች እና የአስተማሪዎችን ዳሰሳ ውጤቶችን ጭምር ይገልጻል። በተጨማሪ፣ በእያንዳንዱ ሪፖርት ካርድ ላይ፣ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በአሁን ጊዜ ትምህርት ቤቱ አሠራሩን አሻሽሎ እንደሆነ በእያንዳንዱ አመላካች ላይ ይታያል። ለመጪዎቹ ዓመታት፣ የሜሪላንድ ሪፖርት ካርድ ስለ 8ኛ ክፍል የማህበራዊ ጥናት ምዘናን ጭምር ያካትታል።

የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ጃክ ስሚዝ/Superintendent of Schools Jack Smith ባለፈው ዓመት እንደገለጹት፣ የሜሪላንድ ሪፖርት ካርድ ስለትምህርት ቤቶቻችን ስፈላጊ መረጃ የሚሰጥ ቢሆንም፣ ስለ 165,000 በላይ የሆኑ ተማሪዎቻችን እርምጃ የሚያሳዩት ውስን ነው።

ትምህርት ቤቶቻችን ሁሉንም ተማሪዎቻችንን እንዴት እንደሚያገለግሉ በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት እንዲያስችል፣ MCPS . ፍትኃዊ የአካውንቴብሊቲ ሞዴል/Equity Accountability Model አጠናቅሯል። ይህም ስለ ትምህርት ቤት ውጤታማነት የበለጠ ዝርዝር እና ትኩረት ያለው ሪፖርት ይሰጣል፤ ፍትኃዊ የአካውንቴብሊቲ ሞዴል በርካታ እና ዘወትር የሚካሄዱ ምዘናዎችን የተማሪዎችን እርምጃ (እየተሻሻሉ መሄድ)፣ ስለ ተማሪዎች ስኬት ልዩነት/አለመጣጣም መቀነስ እና ማስወገድ ልዩ ትኩረት በመስጠት ትምህርት ቤት የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት ያሟላ እንደሆን ለመወሰን ይጠቅማል።

ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎ ሳያመነቱ ያነጋግሩኝ

ከልብ የሆነ

Michael Burd
Principal